ትምህርተ ሥላሴን አስመልክቶ ተዘውትረው ከሚጠየቁ ጥያቄዎች መካከል የጥቂቶቹ መልስ

ከተስፋዬ ሮበሌ

በዚህ ጽሑፍ ሰዎች ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ አዘውትረው ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ። እነዚህ ጥያቄዎች በርእሰ ጉዳዩ ላይ በማስተምርባቸው ቦታዎች እንዲሁም በደብዳቤ ከደረሱኝ ጥያቄዎች መኻል ትልቅ ቦታ ይይዛሉ እንዲሁም አግባብ የሆነ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል ከምላቸው መኻል ዋነኞቹ ናቸው። ለእነዚህ ጥያቄዎች የምሰጠው ምላሽ አስተምህሮተ ሥላሴን በተሟላ መልኩ ያብራራል ማለት እንዳልሆነ ግን አንባብያን እንዲረዱኝ እፈልጋለሁ። በአስተምህሮው ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ እኔ ከወንድም አማረ መስፍን ጋር የዘጋጀሁትና በቅርቡ ለንባብ የሚበቃውን መጽሐፍ፣ "የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ" (650 ገጽ) እንዲሁም እኔ የዘጋጀኋቸውን የሚከተሉትን ሦስት መጻሕፍት ይመለከታል፦ "የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት" (150 ገጽ)፣ "ሰባልዮሳውያን—የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን" (250 ገጽ) እንዲሁም "የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን" (180 ገጽ) የሚለውን መጽሐፍ እንዲያነቡ ልባዊ ምክሬ ነው። ተጨማሪ ጥያቄም ሆነ አስተያየት ካልዎ የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045፣ ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ወይም በኢሜል <tesfa_apologetics@yahoo.com> ብለው ቢጽፉልኝ ይደርሰኛል። መልካም ንባብ!

1. "ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ፣ 'እኔ አምላክ ነኝ' ለምን አላለም?"

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን በግልጽና በስፋት የሚያስተምሩ ቢሆንም፣ አንዳንድ ሰዎች ቃል በቃል ኢየሱስ፣ "እኔ አምላክ ነኝ" ለምን አላለም? ኢየሱስ ይህ ዐይነቱን ንግግር በግልጽ ተናግሮ ቢሆን ኖሮ ወይም "የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነኝ" ቢል ኖሮ፣ አምላክነቱን መቀበልም ሆነ ትምህርተ ሥላሴን ማመን አዳጋች አይሆንም ነበር ይላሉ። በመሠረቱ በሐዲስ ኪዳን ምንባባት፣ ይህ ዐይነቱ ንግግር ቃል በቃል ተጠቅሶ አለመገኘቱ እሙን ቢሆንም፣ በጽሐፍ ቅዱስ በራሱ የአገላለጽ መንገድ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጽና በስፋት ያስተምራል። ለዚህ ጥያቄ ከሚቀርቡ አጥጋቢ መልሶች መኻል የሚከተሉት አራት ነጥቦች ትልቅ ቦታ ሊሰጣቸው የሚገባ ይመስለኛል፦—

አንደኛ፣ ትምህርተ ሥላሴንም ሆነ የክርስቶስን አምላክነት የማይቀበሉ ሰዎች፣ ኢየሱስ በቀጥታ፣ "እኔ አምላክ ነኝ"፣ "እኔ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነኝ" ወዘተ እስካላለ ድረስ፣ አምላክነቱን መቀበል ያዳግተናል የሚሉ ከሆነ፣ ከእዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የአመክንዮ አካሄድ በመከተል ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል፦— "እኔ አምላክ አይደለሁም"፣ "እኔ የሥላሴ ሁለተኛ አካል አይደለሁም" ብሎ ስላልተናገረ አምላክነቱንም ሆነ የሥላሴ አካል መሆኑን ሰዎች ሊቀበሉ ይገባል ማለት ይቻላልን? ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በቃል፣ "እኔ አምላክ ነኝ" ያለማለቱ አምላክ ያለመሆኑን እንደማያሳይ ሁሉ፣ "እኔ አምላክ አይደለሁም" ብሎ እስካልተናገረም ድረስ አምላክ ነው ወደሚል ድምዳሜ መሄድ አይቻልም። ከዚህ የምንማረው እውነት ቅዱሳት

መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ አምላክነት ወይም ስለ ትምህርተ ሥላሴ የሚያስተምሩት ትምህርት፣ የእኛን የዐረፍተ ነገር አካሄድ ወይም የትንታኔ ዘዴ በተከተለ መልኩ እንዳልሆነ ነው።

በአንድ ወቅት በክርስቶስ አምላክነት ላይ እንወያይ የነበረ አንድ የይሖዋ ምስክር፣ "እኔ ኢየሱስን ሁሉን ቻይ አምላክ አድርጌ የማልቀበልበት ምክንያት፣ ኢየሱስ በቀጥታ 'እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ' ብሎ ስላልተናገረ ነው" አለኝ። እኔም "ከዚህ ንግግርህ የተረዳሁት፣ አንድ ትምህርት ትክክል ነው ብለህ የምታምነው፣ ትምህርቱ ቃል በቃል አንተ በምትፈልገው መልክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ ሲገኝ ነው ማለት ነው?" ስል ጥያቄ አቀረብሁለት። እርሱም በሙሉ ልብ ቄፍጠን ብሎ፣ "እንዴታ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ አማኒ እንደ መሆኔ መጠን መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል ያልነገረኝን ነገር አላምንም" አለኝ። እኔም፣ "እንግዲያው መጽሐፍ ቅዱስ 'ኢየሱስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው' ወይም ' ኢየሱስ አምላክ ለሥራ ሲነሣሣ በመጀመሪያ የፈጠረው ፍጡር ነው' የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት አሳየኝ" አልሁት፤ እርሱም ጥቂት ካሰበ በኋላ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃለ፣ 'ኢየሱስ ሚካኤል ነው' ባይልም፣ ይህ ዐይነቱ ሐሳብ ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ" አለኝ። መጽሐፍ ቅዱስ ቃል በቃል፣ "ኢየሱስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው" ወይም "ኢየሱስ አምላክ ለሥራ ሲነሣሣ በመጀመሪያ የፈጠረው ፍጡር ነው" በማይልበት ሁኔታ፣ "ይህ ዐይነት ሐሳብ ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ" በሚል፣ "ኢየሱስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው"፣ "ኢየሱስ አምላክ ለሥራ ሲነሣሣ በመጀመሪያ የፈጠረው ፍጡር ነው" ብለህ የምታምን ከሆነ፣ "ቃል በቃል ካልተጠቀሰ አላምንም" የሚለው አቋምህ ከዚህ ሐሳብ ጋር እንዴት ታስታርቀዋለህ አልሁት። የዚህ ጽሑፍ አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባ ቀሥም ነገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ አንድን ሐሳብ ቃል በቃል እኛ በምንፈልገው መልክ አልተናገረውም (አላቀረበውም) ማለት፣ ከዚህ ተቃራኒው ሐሳብ ትክክል ነው ማለት አይደለም።

ሁለተኛ፣ የክርስቶስን አምላክነት የማይቀበሉ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት የተለየ ትንታኔ ይሰጧቸዋል። ለምሳሌ፦— የይሖዋ ምስክሮች ዮሐንስ 1÷1፤ 1÷18፤ 20÷28 ላይ ኢየሱስ በግልጽ "አምላክ" እንደ ተባለ የሚቀበሉ ቢሆንም[1]፣ "አምላክ መባሉ አምላክ መሆኑን የሚያስተምር ሳይሆን፣ የአምላክ እንደራሴ/ወኪል መሆኑን የሚያሳይ ነው" የሚል ትንታኔ ያቀርቡለታል። ከዚህ የምንማረው እውነት ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ/ቃል በቃል፣ "እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ"፣ "እኔ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነኝ" ቢል እንኳ፣ ለዚህ አነጋገሩ የተለየ ትንታኔ በመስጠት፣ "'ኢየሱስ፣ እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ' ማለቱ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን ወይም የሥላሴ ሁለተኛ አካል መሆኑን ለማስተማር ሳይሆን፣ በውክልና ደረጃ አምላክ ተብሎ መሰየሙን ለማስረዳት ነው" የሚል ወይም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ትንታኔ ይቀርብለት እንደ ነበር መገመት አዳጋች አይሆንም። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በቃል፣ "እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ"፤ "እኔ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ነኝ" ቢልም ንግግሩ ለትርጓሜ አማራጭ ትንታኔ አይበጅለትም ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው። ከዚህ የምንማረው ጉዳይ አንድ ነገር እኛ በምንፈልገው መልኩ በቀጥታ መጠቀሱም ሆነ ያለመጠቀሱ፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያለውን ክርክር የሚያስወግድ አይሆንም[2]።

---

[1] በቅርቡ ከአስተምህሮአቸው ጋር እንዲጣጣም በማሰብ፣ በአማርኛ ቋንቋ ተርጉመው ለንባብ ያቀረቡት የሐዲስ ኪዳን ቅጅ፣ በእነዚህ ክፍሎች ኢየሱስ አምላክ እንደ ተባለ ይህም ኢየሱስ ለአብ ያለውን ውክልና እንደሚያሳይ ይገልጻል።

[2] እኔና ወንድም አማረ መስፍን ትምህርተ ሥላሴን በማስተምርበት ወቅት፣ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ሰዋስዋዊ ሙግት ማቅረብ ስለነበረብኝ በዮሐንስ 1÷1 ላይ የሚከተለውን ሙግት ዐቀረብሁ፦— ዮሐንስ 1÷1 ላይ "ጋር" ወይም "ዘንድ" ተብሎ በአማርኞቹ ቅጆች ላይ የተተረጐመው የግሪክ ቃል ("ፕሮስ" "πρὸς")፣ በእንግሊዝኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ላይ የተተረጐመው "with"

ሦስተኛ፤ ከወንጌላት የምንማረው ትምህርት የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ቀዳማይ ተልእኮ አብን መግለጥ፣ አብን ማክበር እንዲሁም ሰዎችን ከአብ ጋር ማስታረቅ ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:— ማቴዎስ 11÷27፤ ዮሐንስ 14÷6፤ 17÷4)። ሐዋርያው ጳውሎስም የኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳማይ ተልእኮ ራሱን እንደ ባርያ ዝቅ በማድረግ እግዚአብሔርን ማስከበር እንጂ፣ ራሱን ከፍ ማድረግ አይደለም (ፊልጵስዩስ 2÷6-7 ጳውሎስ ይህን ንግግር የተናገረው ክርስቲያኖች እርስ በርስ መከባበር እንዳለባቸው ባስተማረበት ዐውድ ነው)። ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ አምላክ ነኝ ቢል ኖሮ የመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የነበሩ አይሁድ ጐዳዩን እንደ ትልቅ ዕብደት ይቈጥሩት ነበር። ስለዚህ ማንነቱን አለዝቦ ደቀ መዛሙርት በሂደት የክርስቶስን ማንነት፣ ሕይወትና ትምህርት በመመልከት ወደዚህ ድምዳሜ እንዲደርሱ እንደ ፈለገ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል።

አራተኛ፤ ይህ እውን በሆነበት ሁኔታ እንኳ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ራሱን ሁሉን ቻይ አምላክ አድርጎ ያቀረበባቸው በርካታ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት አሉ። ከዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን እንመልከት:—

ሀ. ***ኢየሱስ አምላካዊ ክብር አለው።*** ኢየሱስ ሰዎች አብን እንደሚያከብሩ ሁሉ እርሱንም እንዲያከብሩ አስተምሮአል (ዮሐንስ 5÷23)። ሃይማኖታዊ ስግደትን በሚያመለክትበት ዐውድ ውስጥ፣ ኢየሱስ አምላካዊ ስግደት ተቀብሎአል (ማቴዎስ 14÷33፤ 28÷17)። ጸሎታቸውን ስምቶ ምላሽ በሚሰጥበት ሁኔታ ውስጥ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ እንዲጸልዩ አስተምሮአል (ዮሐንስ 14÷14)። ኢየሱስ ሰዎች እግዚአብሔር አብን እንደሚያምኑት ሁሉ በእርሱም ላይ እምነት እንዲኖራቸው አበረታቶአል (ማቴዎስ 9÷28፤ ዮሐንስ 14÷1)። ኢየሱስ ሰዎች ከሥጋ ዘመዶቻቸው ይልቅ እርሱን መውደድ እንዳለባቸው አስተምሮአል (ማቴዎስ 10÷37፤ ሉቃስ 14÷26፤ ዮሐንስ 14÷15:21፤ 15÷10)።

ለ. ***ኢየሱስ አምላካዊ ባሕርይ አለው።*** ኢየሱስ ልክ እንደ አባቱ ስለሆነ እርሱን ማየት ማለት አባቱን እንደ ማየት እንደ ሆነ ተናግሮአል (ዮሐንስ 14÷7-10)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በሚገኙበት ስፍራ ሁሉ እንደሚገኝ (አነዜ/መላኤ ኩሉ) እንደ ሆነ ተናግሮአል (ማቴዎስ 18÷20፤ እንዲሁም የሚከተለውን ክፍል ይመለከቷል ማቴዎስ 28÷20)። ኢየሱስ ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት እንደ ነበር ተናግሮአል። ይህ ደግሞ ጅማሮ የሌለው፣ ዘላለማዊ የሆነ አምላክ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው (ዮሐንስ 8÷58-59፤ 17÷5)። በብሉይ ኪዳን ያህዌ "እኔ እኔ ነኝ" እንዳለው ሁሉ ኢየሱስም "እኔ እኔ ነኝ" ብሎአል (ዮሐንስ ፤ 4:26፤ 6:20፤ 8:24:28:58፤ 13:18-19፤

ተብሎ ነው። በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ሰዋስው፣ "ፕሮስ" "πρὸς" የሚለው ቃል በተሳቢ ሙያ (objective case) በሚቀደምበት ጊዜ መስተጋብርን/ግንኙነትን ያመለክታል፤ ይህ ደግሞ ወልድ በአብ ውስጥ ያለ ንግረተ ቃል ሳይሆን ከአብ ጋር አብሮ የሚኖር አካል መሆኑን ያሳያል። በዚህ የትምህርት ፕሮግራም አዘውትሮ ወደ ጉባኤው ይመጣ የነበረ አንድ ሰው፣ "ዮሐንስ 1÷1 ላይ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ለመግለጽ ቢፈልግ ኖሮ፣ በዚህ ክፍል "ፕሮስ" "πρὸς" ከሚለው የግሪክ ቃል ይልቅ "ፓራ" "παρά" የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀም ነበር። ስለዚህ "ፓራ" "παρά" ከሚለው ቃል ይልቅ "ፕሮስ" "πρὸς" የሚለው የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ መዋሉ አብም ወልድም ኢየሱስ መሆኑን ያሳያል" የሚል ሙግት ዐቀረበ። እኔም የሙግት አካሄድህ የተሳሳተ ነው ስል ግለሰቡን ተቃወምሁ። ሙግትህ፣ "ፕሮስ" "πρὸς" ከሚለው ቃል ይልቅ "ፓራ" "παρά" የሚለው ቃል በቦታው ላይ ተጠቅሶ ቢገኝ ይሻለኛል ሳይሆን፣ ተጠቅሶ የተገኘው ቃል ("ፕሮስ" "πρὸς") በተሳቢ ሙያ ሲቀደም ግንኙነትን ያሳያል ወይስ አያሳይም የሚል ሙግት ነው ማቅረብ የሚኖርብህ አልሁት። ምክንያቱም "ከዚህ ቃል ይልቅ ይህ ቃል ቢጠቀስ ይሻለኛል" የሚለው የግለሰቡ የሙግት አካሄድ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እኔ በፈለግሁበት መንገድ ካልተጻፈ፣ ልቀበለው እቸገራለሁ" የሚለውን መቅድመ እሳቤ በቅድመ ሁኔታ ያስገባ ስለሆነ።

18:5-8፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሩ ዘዳግም 32÷39፤ ኢሳይያስ 41÷4፤ 43÷2:5:10-11:25፤ 46÷4፤ 52÷6)::

ሐ. ***ኢየሱስ አምላካዊ ግብር አለው::*** ኢየሱስ ክርስቶስ ከተፈጥሮ ሕግጋት ሁሉ በላይ እንደ ሆነ ተናግሮአል:: ይህ ደግሞ በብሉያት አብ የተፈጥሮ ሕግጋት ጌታ የሆነበትን ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ማቴዎስ 8÷23-27፤ 14 ÷13-33፤ ከሚከተሉት ክፍሎች ጋር ያነጻጽሯል መዝሙር 77÷16-20፤ 104÷4-9፤ 107÷23-30):: ልክ እንደ አብ ሥልጣናዊ ቃል ይናገራል:: እንደ ነቢያት "የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ሳይሆን፣ "እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ" የሚለውን ንግግር ብሉያት ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር በማነጻጸር ተናግሮአል (ለምሳሌ ማቴዎስ 5÷18:26፤ ማርቆስ 3÷28፤ ሉቃስ 4÷24፤ ዮሐንስ 1÷51):: የሰዎችን ኀጢአት ይቅር እንደሚል አስተምሮአል (ማቴዎስ 9÷1-8፤ ማርቆስ 2÷1-12፤ ሉቃስ 5÷17-26):: ለሙታን ሕይወት እንደሚሰጥ ተናግሮአል (ዮሐንስ 5÷28-29፤ 11÷25-26):: ለወደደው ሕይወትን ይሰጣል (ዮሐንስ 5÷21-26):: በመጨረሻም በሰዎች ዕጣ ፈንታ ላይ ሁሉ ይፈርዳል (ማቴዎስ 16÷27፤ 25÷31-46፤ ዮሐንስ 5÷22-23):: መንፈስ ቅዱስን ከሰማይ የመላክ ሥልጣን እንዳለው ተናግሮአል (ዮሐንስ 15÷26፤ 16÷7-14)::

መ. ***ኢየሱስ አምላካዊ መንበር አለው::*** ኢየሱስ በጽንፈ ዓለሙ ሁሉ ላይ ሥልጣን እንዳለው (ማቴዎስ 28÷18):: ስለዚህም በአምላክ ሉዓላዊ ዙፋን ላይ መቀመጥ ይችላል (ማቴዎስ 25÷31፤ ማርቆስ 12÷36፤ ሉቃስ 20÷42-43):: በሁሉ ላይ የበላይ ባለሥልጣን ነው (ማቴዎስ 11÷25-27፤ ሉቃስ 10÷21-22፤ ዮሐንስ 3÷35፤ 13÷3፤ 16÷15):: ከዚህም የተነሣ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ምግባሩና ንግግሩ ራሱን ከአምላክ ጋር የሚያስተክክል ነው በሚል የከሰሱት (ማቴዎስ 9÷3፤ ማርቆስ 2÷7፤ 14÷61-64፤ ዮሐንስ 5÷17-18፤ 8÷58-59፤ 10÷27-33፤ 19÷7):: ኢየሱስ ራሱን እንኳ የማስነሣት ችሎታ እንዳለው አስተምሮአል (ዮሐንስ 2÷19-22፤ 10÷17-18)::

ሠ. ***ኢየሱስ አምላካዊ ስም አለው::*** ቶማስ "ጌታዬና አምላኬ" (ዮሐንስ 20÷28) ብሎ ኢየሱስን መናገሩ ኢየሱስ አንተ የትንሣኤ ጌታ መሆኔን ስላየህ አምነሃል ሳያዩ የሚያምኑ ምስጉኖች ናቸው ሲል የሰጠው ምላሽ፣ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን አምላኬና ጌታዬ ብለው እንዲያምኑት የሚያሳስብ ነው (ኢየሱስን "አምላክ" የሚሉ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ዮሐንስ 1÷1:18፤ ሮሜ 9÷5፤ 1ዮሐንስ 5÷20-21፤ ዕብራውያን 1÷8፤ ሐዋርያት ሥራ 20÷28፤ ቲቶ 2÷13፤ 2ጴጥሮስ 1÷1)::

ኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ፣ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ፣ ስግደትና አምልኮ የሚገባው፣ ሁሉን የሚችል፣ በሁሉ ቦታ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምር ከሆነ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ቶማስ፣ "አምላኬና ጌታዬ" ብዬ ማመኔ መጽሐፍ ቅዱስን የተከተለ አምልኮ የማይሆንበት ምክንያቱ ምንድን ነው?

፪. "የሥላሴ አስተምህሮ ትክክል ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፊ ማብራሪያ ለምን አይሰጥም?"

ትምህርተ ሥላሴን የማይቀበሉ ሰዎች፣ አብዝተው ከሚያቀርቧቸው የሙግት ነጥቦች መኻል አንዱ፣ መንፈስ ቅዱስ ሊገኝባቸው በሚገቡ በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ውስጥ ተጠቅሶ አይገኝም:: ትምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ቢሆን ኖሮ አብና ወልድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት እንደ ተጠቀሱት፣ መንፈስ ቅዱስም ተጠቅሶ ይገኝ ነበር የሚል ነው:: ለዚህ ሙግት ማጠናከሪያ በግብአትነት ከሚውሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች መኻል የሚከተሉት ክፍሎች ትልቁን ቦታ ይይዛሉ (ሮሜ 1÷7፤ ማቴዎስ 11÷27፤ ማርቆስ 13÷32፤ ሐዋርያት ሥራ 7÷55-56)::

በሐዋርያው ጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ፣ ሐዋርያው በሰላምታው ውስጥ አብና ወልድን ሲጠቅስ መንፈስ ቅዱስን አልጠቀሰም፣ "ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን" (ሮሜ 1÷7)። አብና ወልድ የተለያዩ አካላት እንደ ሆኑ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም የራሱ ማንነት ያለው አካል ቢሆን ኖሮ በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀስ ይገባ ነበር። ኢየሱስ፣ "ከአብ ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድና ወልድ ራሱ ፈቅዶ ከሚገልጥላቸው ሌላ አብን የሚያውቅ የለም" (ማቴዎስ 11÷27) በሚለው ንግግሩ ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስን አላካተተም። መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ ህልውና ያለው አምላክ ቢሆን ኖሮ አብና ወልድን እንደሚያውቅ፣ አብና ወልድም መንፈስ ቅዱስን እንደሚያውቁ መጠቀስ ነበረበት። ኢየሱስ፣ "ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክትም ሆኑ፣ ወልድም ቢሆን፣ ምንም አያውቅም" (ማርቆስ 13÷32) በሚለው ንግግሩ ውስጥ፣ "ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በስተቀር" የሚለውን ንግግር መናገር ነበረበት። የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን በራእያቸው ውስጥ አበና ወልድን እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስን እንደ ተመለከቱ አንዳችም ጊዜ አልተጠቀሰም (ሐዋርያት ሥራ 7÷55-56)።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ ይህን ጥያቄ የሚጠይቁ ሰዎች እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት በተብራሩበት መልኩ፣ አብና ወልድ ተጠቅሰው መንፈስ ቅዱስ ያልተጠቀሰባቸውን ክፍሎች በማሳየት፣ መንፈስ ቅዱስ ያለመጠቀሱ ያለመኖሩን የሚያመለክት ነው ለሚል ትንታኔ ይዳረጋሉ።

ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ቀዳማይ መሪነት እንደ ተጻፉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (1ጴጥሮስ 1÷21)። እንዲሁም የሥላሴ አካላት አንዱ የሌላውን ክብር እንደሚሻና መንፈስ ቅዱስም የአብንና የወልድን ክብር እንደሚፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል፣ "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል" (ዮሐንስ 16÷13-14)። ከእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች የምንማረው ቀሩም ነገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ መጽሐፍ ከሆነ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ አብና ወልድን ማክበር እንጂ ራሱን ከፍ ማድረግ ዐላማው ካልሆነ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳማይ ጠንሳሽነት የተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት አብና ወልድን ማክበር ቀዳማይ ዐላማቸው ቢሆን ሊያስደንቀን አይገባም። ርእሰ ጉዳዩን ግልጽ ያደርገው ከሆነ አንድ ምሳሌ ልጠቀም። እኔ ከሁለቱ ልጆቼና ከባለቤቴ ጋር ወደ ሶደሬ ለመዝናናት ሄድን እንበል። ከቤተ ሰባችን አባላት መካከል አንዱ ፎቶ ሲያነሣ፣ የተቀረነው ፎቶ ይነሣል። በተለይ ፎቶዎቹ ታጥበው ሲመጡ በብዙ ፎቶዎች ላይ እኔ የለሁም፤ ይህ የሆነበት ምክንያት በርካታ ፎቶዎችን ያነሣሁት እኔ ስለሆንሁ እንጂ እኔ በቦታው ስላልነበርሁ አይደለም። በአብዛኞቹ ፎቶዎች ላይ አልታየሁም ማለት የለሁም ነበር ማለት አይደለም።

ካልተጠቀሰ የለም የሚለውን የሙግት አካሄድ፣ የሥነ አመክንዩ ምሁራን፣ "አርጊውመንተም ኤክስ ሳይለንሺዎ"[3] በማለት የሚጠሩት ስሑት ሙግት ነው። ይህ ሙግት፣ "መኖሩ ካልተጠቀሰ የለም ማለት ነው" በሚለው አባዜ የተለከፈ ነው። ጸሓፊው ወይም ተናጋሪው ይጠቀስ የተባለውን አካል ወይም ርእሰ ጉዳይ ያለመጥቀሱ ብዙ አማራጭ ምክንያቶች ሊቀርቡለት ይገችላል [ለምሳሌ (1) ጸሓፊው ከሚጽፍበት ዐላማ አንጻር መጥቀስ የሚፈልገውን ብቻ መጥቀሱ ያልጠቀሰው ነገር ሁሉ የለም ማለት ወደሚለው ድምዳሜ መሄድ ስሕተት ነው። (2) ጸሓፊውም

[3] argument from silence (*argumentum ex silentio).*

ሆነ ተናጋሪው አንድን ነገር የሚነግሩን በጉዳዩ ላይ ካላቸው መረዳት አንጻር ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። (3) ጸሓፊው ወይም ተናጋሪው ጉዳዩን ቀዳማይ ተደራሲያኑ ወይም የንግግሩ አድማጮች ጠንቅቀው ያውቁታል ስለዚህም ጉዳዩን መጥቀሴ አስፈላጊ አይደለም ብሎ አስቦ ሊሆን ይችላል]። ጉዳዩ ያለመጠቀሱ በርካታ አማራጭ ሐሳቦች በሚቀርቡለት ሁኔታ "ያለመጠቀሱ ያለመኖሩን የሚያሳይ ነው" ማለት ስሕተት ነው።

ይህ ዐይነቱ የሙግት አካሄድ ቅዱሳት መጻሕፍትንም ሆነ ነገረ መለኮትን በምናጠናባቸው ጊዜያት አብዝተው የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ድንግል ስለመፀነሷ አንዳችም ጊዜ አልተናገረም፤ ይህ ማለት ድንግል መፀነሷን አያምንም ነበር ወይም አያውቅም ነበር ማለት አይደለም። ዮሐንስ ወንጌል 20÷1 መግደላዊት ማርያም ወደ መቃብሩ ስፍራ እንደሄደች ሲገልጽ፣ ማርቆስ 16÷1 ደግሞ፣ "መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ" አብረው እንደ ሄዱ ገልጸአል። ማቴዎስ 28÷1 ደግሞ፣ "መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም" ወደ መቃብር እንደ ሄዱ ገልጸአል። ዮሐንስ ያልነገረንን ጉዳይ ማርቆስና (የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ) ማቴዎስ (ሁለተኛዪቱ ማርያም) መንገራቸው ክፍሎቹ ተደጋጋፊ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ዮሐንስ መግደላዊት ማርያምን ብቻ መጥቀሱ፣ ሌሎቹ ሰዎች የሉም ማለቱ አይደለም። ዮሐንስ በመልእክቱ ውስጥ ያልንገረንን ነገር ሌሎቹ የወንጌል ጸሓፊዎች በዝርዝር ነግረውናል፤ ነገር ግን ሌሎቹ የወንጌል ጸሓፊዎች የነገሩንን ነገር ዮሐንስ ያለመናገሩ ጉዳዩን አያውቀውም ወይም ጉዳዩ የለም ማለት አይደለም[4]። ኢየሱስ ክርስቶስ በነበረበት ዘመን የነበረው ስመ ጥሩ አይሁዳዊ የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (Josephus) በጽሑፎቹ ውስጥ ሁሉ አንድም ጊዜ እንኳ ናዝሬትን አልጠቀሰም። ይህ ማለት ናዝሬት እርሱ በነበረበት ዘመን አልነበረችም ማለት አይደለም።

በርካታ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት አብና ወልድን የጠቀሱትን ያህል መንፈስ ቅዱስን ጠቅሰው ያለመገኘታቸው እሙን ነው። ይህ ማለት ግን መንፈስ ቅዱስ የሚባል አካል የለም ማለት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሰላምታው ውስጥ መንፈስ ቅዱስን ባይጠቅስም ሐዋርያው ጴጥሮስ በሰላምታው ውስጥ መንፈስ ቅዱስን ከአብና ከወልድ ጋር አያይዞ ጠቅሶአል፣ "***እግዚአብሔር አብ*** አስቀድሞ ካወቃቸው፣ ***ኢየሱስ ክርስቶስን*** ለመታዘዝ በደሙ ለተረጨችና ***በመንፈስ*** አማካይነት ለተቀደሱት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ" (1ጴጥሮስ 1÷2)። ይህ ጳውሎስ በሰላምታ ውስጥ ያልጠቀሰውን ነገር ጴጥሮስ ጠቅሶ መገኘቱ ጳውሎስ ያለጠቀሱ ሌላ ትንታኔ የሚቀርብለት እንጂ ያለመኖሩን የሚያሳይ ነው ብሎ ድምዳሜ መስጠት ስሕተት ነው። ለምን አልተጠቀሰም ለሚለው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ የሆነ መልስ ስላልሰጠን መልስ ናቸው የምንላቸው ሁሉ ከግምት የሚያልፉ አይሆንም።

አንዳንድ ምሁራን መንፈስ ቅዱስ ለምን አልተጠቀሰም ለሚለው ጉዳይ፣ "የአብና ወልድን ሰላምታ በአማኙ ልብ ውስጥ የሚያፈሰው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ እንዲሁም አማኞች በውስጣቸው በሚሠራው ሥራ መንፈስ ቅዱስን ስለሚያውቁት ነው" የሚል አስተያየት አላቸው። አንዳንዶች ደግሞ ጳውሎስ በሰላምታው ውስጥ አብና ወልድን ብቻ መጥቀሱ፣ ሐዋርያው በመልእክቶቹ ውስጥ ሊያንሸራሽራቸው የሚገቡ ሐሳቦችን ለማስተላለፍ አብና ወልድን ብቻ መጥቀሱ በቂ ስለሆነ ነው ይላሉ። እነዚህ አስተያየቶች ምን ያህል አጥጋቢ ናቸው የሚለው ጉዳይ ከሰው ሰው የሚለያይ ቢሆንም በእርግጠኝነት የምንረዳው ጉዳይ፣ "ያለመጠቀስ

[4] ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንዳን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይቃረናል ለሚለው ሙግታቸው ይህ ዐይነቱን የሙግት አካሄድ ሲጠቀሙ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይቃረናልን በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ በቅርቡ፣ የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ ከወንድም አማረ መስፍን ጋር፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይቃረናልን?" በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ ይመለከታል።

ያለመኖርን የሚያመለክት እንዳልሆነ" ነው። ይህ ደግሞ የጳውሎስ ሰላምታ የመንፈስ ቅዱስን ያለመኖር የሚያስተምር አይደለም።

"ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር አብና ስለራሱ ባስተማረባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማስተማር ነበረበት" የሚል አስተያየት ስላላቸው፣ አንባብያን ሁለት ጉዳዮችን ልብ እንዲሉ ያስፈልጋል፦—

(1) ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ስለ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ መረዳት የሚችሉት በበዓለ ኀምሳ ቀን ወደ ሕይወታቸው መጥቶ በውስጣቸው መኖር በሚጀምርበት ጊዜ ነው የሚል አስተሳሰብ እንደ ነበረው ከወንጌላቱ ትምህርት መረዳት ይቻላል። ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በስፋት ያተናገረው ታልፎ በሚሰጥበት ሌሊት ነው (ዮሐንስ 14-16)። በዚሁ ዐውድ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት እርሱ የሚለውን ነገር ሁሉ በግልጽ መረዳት የሚችሉት፣ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አብሮአቸው መኖር ሲጀምር እንደ ሆነ ገልጾአል (ዮሐንስ 14÷25-26፤ 16÷13-14)። ይህ ጉዳይ ስለ መንፈስ ቅዱስ መረዳት የሚቻለው እርሱ ሲመጣና ማንነቱን ለሐዋርያቱ ግልጥልጥ አድርጎ ሲነግራቸው ብቻ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "ወልድን የሚያውቀው አብ ብቻ ነው" (ማቴዎስ 11÷27) ለምን አለ የሚለውም ጉዳይ መታየት ያለበት ከዚሁ አንጻር ነው። ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ይህን ከመናገሩ በፊት መንፈስ ቅዱስን የማያውቁ ከሆነ፣ "ወልድን የሚያውቁት አብና መንፈስ ቅዱስ ናቸው" የሚል ንግግር በዚህ ዐውድ ውስጥ ሊያስገባ ይችላልን? ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ "ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክትም ሆኑ፣ ወልድም ቢሆን፣ ምንም አያውቅም" (ማርቆስ 13÷32) በሚለው ቦታ መንፈስ ቅዱስን ቢያካትት ኖሮ አድማጩን ከማደናገር ውጪ ንግግሩ በአድማጮቹ ዘንድ አንዳችም እርባና ሊኖረው አይችልም።

(2) "ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክትም ሆኑ፣ ወልድም ቢሆን፣ ምንም አያውቅም" (ማርቆስ 13÷32) በሚለው ምንባብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም። ነገሩን ግልጽ የሚያደርገው ከሆነ አንድ ምሳሌ ላቅርብ። የአንድ ድርጅት አስተዳዳሪ የሆኑ ሰው ለድርጅቱ ምክትል አስተዳዳሪ፣ "በፊታችን ባሉት ሳምንታት ሥራዬን ለመልቀቅ ወስኛለሁ፤ ይህን ምስጢር ማንም ሰው አያውቅም፤ አንተም ለማንም እንዳትናገር" ቢሉ፣ "ይህን ምሥጢር ማንም ሰው አያውቅም" የሚለው አነጋገራቸው የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞች ብቻ ታሳቢ ያደረገ እንጂ፣ የግለሰቡን ሚስት እንዲሁም ቤተሰብ ስለ ጉዳዩ አንዳችም ዕውቀት የላቸውም ማለት ላይሆን ይችላል። መስማት ካለባቸው ሰዎች ውስጥ ያልሰሙትን ሰዎች እንጂ መስማተ ካለባቸው ሰዎች መኻል የሰሙትን ሰዎች የሚያከትት አይደለም። ግለሰቡ "ባለቤቴ፣ ልጄና፣ በአሜሪካ አገር ያለው ታላቅ ወንድሜ በስተቀር" ወዘተ ማለት አያስፈልጋቸውም። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ስላልሆኑ የመሥሪያ ቤቱ ዐውድ ሊሆኑ አይችሉም። ልክ እንደዚሁ ሁሉ በማቴዎስ 11÷27 እና በማርቆስ 13÷32 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ መጥቀስ አንዳችም ጠቀሜታ የለውም።

"በራእይ እግዚአብሔርን የተመለከቱ ሰዎች፣ ኢየሱስንና አብን እንጂ መንፈስ ቅዱስን አልተመለከቱም፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተለየ አካል እንዳልሆነ የሚያመለክት ነው" የሚለው ሐሳብ ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ "ስላልተጠቀሰ የለም" የሚለውን ስሑት የሙግት አካሄድ የተከተለ ነው። ዮሐንስ በራእዩ መጀመሪያ የተመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደ ሆነ ተጠቅሶአል (ራእይ 1÷13-18)። የሥላሴ ተቃዋሚዎች መንፈስ ቅዱስ ስላልተጠቀሰ የለም የሚሉ ከሆነ፣ አብም አልተጠቀሰምና የለም ማለት ነውን? መጽሐፉ አቡቀለምሲሳዊ እንደ መሆኑ መጠን ተእምርታዊ ገለጻዎች ይበዙበታል፤ በዚህ መጽሐፍ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ

በግ ተመስሎ ያታየ ሲሆን (ራእይ 5÷6)፣ አብ ደግሞ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠ ሆኖ ቀርቧል (ራእይ 4÷2:9:10 ወዘተ)። ልክ እንደዚሁ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በትእምርታዊ ገለጻ፣ "በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት" (ራእይ 1÷4) እንዲሁም "ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት" (ራእይ 3÷1፤ 4÷5፤ 5÷6) ተብሎ ቀርቧል። "ሰባት ማናፍስት" የሚለውን ሐረግ ቃል በቃል በመተርጐም ሰባት መናፍት አሉ ማለት ስሕተት እንደ ሆነው ሁሉ፣ ኢየሱስንም ቃል በቃል አራት እግር ያለው በግ የሚባለው እንስሳ ነው ማለት ስሕተት ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ሰባት ቁጥር ፍጽምናንና ሙሉዕነትን የሚያመለክት እንደ ሆነ ልብ ይሏል። ይህም የመንፈስ ልዕልና የሚያሳይ ነው። ኢየሱስ በበግ መመሰሉ ለሰው ልጆች ኀጢአት የከፈለውን የትኪ ሞት የሚያመለክት ነው። "ካልተጠቀሰ የለም" የሚለውን ስሑት የሥነ አመክንዮ አካሄድ ካስወገድን፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምሩን እጅግ በርካታ ትምህርቶች አሉ።

3. "የሥላሴ አስተምህሮ ለድነት አንገብጋቢ ጉዳይ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮውን ግልጽ በሆነ መንገድ ለምን አሳብራራውም?"

ትምህርተ ሥላሴን አስመልክቶ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች መኻል አንዱ፣ "የሥላሴ አስተምህሮ የድነት ቅድመ ሁኔታ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮውን ግልጽ በሆነና በማያሻማ መንገድ ለምን አላቀረበውም" የሚለው ጥያቄ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ይህ ጥያቄ የሚጠይቁ ሰዎች አስተምህሮው ግልጽ የሚሆነው በምን መልኩ ሲቀርብ ነው ተብለው ሲጠየቁ፣ አብዛኞቹ የሚያቀርቧቸው አማራጮች መኻል የሚከተሉት ይገኙበታል፣ "እግዚአብሔር ሥላሴ ነው"፣ "በእግዚአብሔር በባሕርይ አንድ በአካል ደግሞ ሦስት ነው"፣ "አብ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስም አምላክ ናቸው"። በዚህ መልክ በማያሻማ መልኩ ያልቀረቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች በሌሉበት ሁኔታ ትምህርተ ሥላሴ የድነት ቅድመ ሁኔታ ነው እንዴት ሊባል ይችላል?

በመሠረቱ ድነት በነገረ መለኮት ትምህርት በምናገኘው ነጥብ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም። ሃምሳ ከመቶ ያገኙ ሰዎች ዘጠና ከመቶ ካገኙ ሰዎች ይልቅ በአደጋ ላይ ናቸው ወይም ሠላሳ ከመቶ ያገኙ ሰዎች ድነት አላገኙም ማለት በፍጹም አይቻልም። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የነገረ መለኮት ፈተና መውሰድ፣ በዚያም የማለፊያ ነጥብ ማግኘት አይደለም። ማዳን የእግዚአብሔር ድርሻ የሚያድንም እምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚገኝ ነው (ሮሜ 3÷21-26፤ ኤፌሶን 2÷8-10፤ ቲቶ 3÷5-8)። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የሚያድን እምነት ዘወትር ርቱዕ አስተምህሮን የተከተለ ነው። በክርስትና የድነት አስተምህሮ ውስጥ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የድነት ሥራ የማያምኑ ሰዎች ድነት ማግኘት አይችሉም የሚለው ትምህርት፣ ድነት ትክክልኛ አስተምህሮን በቅድመ ሁኔታ ውስጥ ያካተተ ጉዳይ ስለሆነ ነው። በአጠቃላይ ዐበይት በሚባሉ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ላይ የተሳሳተ አቋም ያላቸው ሰዎች ከድነት እንደሚጐድሉ ቃለ እግዚብሔር በግልጽ ያስተምራል (ሮሜ 16÷17-18).። እንዲሁም በደቂቃን/በንዑሳን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይ የተሳሳተ ምልከታ ያላቸው ሰዎች የበሰለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ባለቤት ሊሆኑ አይችሉም (ሐዋርያት ሥራ 18÷25-26)።

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ መልኩ ክርስቲያኖች ስለ ትምህርተ ሥላሴ ማወቅ ያለባቸው ትምህርት የቱ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ "ሥላሴ"፣ "ሦስት አካላት አንድ አምላክ"፣ ወዘተ የሚሉትን ቃላት አይጠቀምም። አንድ ሰው እነዚህን ቃላት መጠቀም አልፈልግም ካለ ያለመጠቀም ሙሉ መብት አለው። ነገረ መለኮታውያን እነዚህን ቃላት የቀመሩት አስተምህሮውን በግልጽ ለማስተማር ከመፈለግ ብቻ ነው። ነገር ግን አንድ ሰው እነዚህ ቃላት

የሚወክሉትን ትምህርት ክዶ መንግሥተ ሰማይ የእኔ ነች ማለት አይችልም። የደቀ መዝሙርነትም ሕይወት ራስን ለሥላሴ ማለትም ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት የሚጀምር ሕይወት ነው (ማቴዎስ 28÷19)። አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አይደለም የሚል እምነት ካለው ከክርስቶስ ጋር ትክክልኛ ግንኙነት ማድረግ አይችለም። ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ" (ዮሐንስ 8÷24) ያለው። ይህ ክፍል የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ማወቅ የድነት ቅድመ ሁኔታ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። እንደ ክርስትና አስተምህሮ ድነት የሚያገኙ ክርስቲያኖች አብ አምላክ፣ ወልድ አምላክ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ ሆነ ማመን ይኖርባቸዋል። ይህን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟሉ ክርስቲያኖች አብ አምላክ ነው፣ ወልድ አምላክ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው የሚለው ትምህርት በሦስት አማልክት ማመን እንዳልሆነ ወይም አንዱ አምላክ ራሱን በሦስት ገጽ/መልክ የገለጸ አምላክ እንዳልሆነ ቢያውቁም መጽሐፍ ቅዱስንና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በማጣቀስ አስተምህሮውን የማብራራት ዕቅም ላይኖራቸው ይችላል። አስተምህሮውን ለአእምሮ በሚገባ መልኩ አላብራሩም ማለት፣ አስተምህሮውን አያምኑም ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መነፈስ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት በትክክል የተረዱ ሰዎች፣ አስተምህሮውን ለአእምሮ ግቡዕ በሆነ መልኩ ለማብራራት የቤተ ክርስቲያን ታሪክንና በተወሰነ ደረጃ የሥነ አመክንዮን አካሄድ ማወቅ ይኖርባቸዋል። በተለይ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይህን አስተምህሮ ለማብራራት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያደረጉትን ጥረት ማወቅ ከእነዚህ አባቶች መኻል አስተምህሮውን ጥሩ በሆነ መልኩ ያብራሩትን ሰዎች አካሄድ በትክክል ስለሚረዳ አስተምህሮውን ለሌሎች ማብራራት የሚከብደው ጉዳይ አይሆንም።

አብዛኞቹ ምናልባትም ሁሉም መናፍቃዊ ትምህርቶች በአስተምህሮተ ሥላሴ ላይ የተዛባ አተያይ አላቸው። ለዚህም ነው የነገረ መለኮት ምሁራን፣ "ትምህርተ ሥላሴ በመናፍቃንና በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መካከል የቆመ የመለያ ሰንደቅ ነው" የሚሉት። በአጠቃላይ እንደ ሥላሴ ያሉ ዐበይት ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን መካድ የዘላለም ዕድል ፈንታችንን ሊወስን አልያም ክርስቲያናዊ ብስለታችንን ሊያጨናግፍ ይችላል። ዐበይት የሚባሉት ክርስቲያናዊ ትምህርቶችም መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ መንገድ በግልጽና በስፋት ያብራራቸው አስተምህሮዎች ናቸው።

4. "አንድ ሰው የሥላሴን አስተምህሮ አይቀበልም የሚባለው የትኛውን ትምህርት ሲክድ ነው?"

ትምህርተ ሥላሴን የማይቀበሉ፣ በአንጻሩ በአስተምህሮው ላይ የተለያየ አመለካከት ላላቸው ሰዎች የሚከተለውን ምክር መምከር እወዳለሁ። ምናልባትም ከሥላሴ አስተምህሮ ይልቅ ኢሥላሴያዊ አመለካከታቸውን ከጥቃት ለመከላከል የሚፈልጉ ነገር ግን ብሉያትና ሐዲሳት ሕጻጽ አልባ የሆኑ፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ/አፈዎተ ቃል ናቸው የሚሉ ሰዎች የሚከተለውን ጥያቄ ራሳቸውን እንዲጠይቁ በእግዚአብሔር ስም እጠይቃለሁ።

1. የአስተምህሮተ ሥላሴ መሠረቶች ናቸው በሚባሉት ነጥቦን የሚቃረኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሙግቶች ያቅርቡ

"የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት" በሚባለው መጽሐፌ ላይ፣ የሥላሴ ትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ባደረገ መልኩ፣ በሚከተሉት ስድስት መሠረተ ነጥቦች ላይ እንደ ተዋቀረ ገልጫለሁ፤ ይኸውም፦—

፩. አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።
፪. ይህ አንዱ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያህዌ በሚል ስያሜ ይጠራ ነበር።
፫. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው እግዚአብሔር አብ አምላክ ነው።
፬. የእግዚአብሔር አብ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርሰቶስ አምላክ ነው።
፭. መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።
፮. አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ አካላት ናቸው።

ትምህርተ ሥላሴ የተሳሳተ አስተምህሮ ነው የሚል አቋም ያላቸው ሰዎች፣ ከእነዚህ ስድስት መሠረተ ነጥቦች መኻል አንድ እንኳ የተሳሳተ መሆኑን ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ አሳማኝ የሙግት ነጥብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ስሕተት ነው የሚለው አቋማቸው ከትምህርተ ሥላሴ ውጪ ካሉ አስተምህሮዎች ጋር ያለው መስተጋብር ምን እንደሚመስል ማሳየት ይኖርባቸዋል። በአጠቃላይ አንድ ሰው የትምህርተ ሥላሴ አስተምህሮ የተሳሳተ ነው ለማለት ከእነዚህ ስድስተ መሠረተ ነጥቦች በኻል ቢያንስ አንዱ ነጥብ ስሕተት ነው በማለት እነዚህ ነጥቦች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው ለሚለው ሙግት የሥላሴ አማንያን ከሚያቀርቡት የተሻለ ማስረጃ ማቅረብ እንዲሁም ሥላሴያውያን እነዚህ መሠረተ ነጥቦች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው ለማለት ከቃለ እግዚአብሔር የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች የተሳሳቱ መሆናቸውን በግልጽ ማሳየት ይኖርባቸዋል።

፪. ግልጽ የሆነ አማራጭ ያቅርቡ

“ትምህርተ ሥላሴን አልቀበልም” ወይም “ትምህርተ ሥላሴ ሰዎች ሊረዱት የማይችሉት ስውር ትምህርት ነው” ማለት ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። ነገር ግን ትምህርተ ሥላሴን ማመን ከሌለብን፣ ማመን ያለብን የትኛውን ትምህርት እንደ ሆነ ሊነገረን ይገባል። የሥላሴ አማንያን የትምህርት የሥላሴ አስተምህሮ መሠረቶች ናቸው የምንላቸውን ከላይ ያየናቸውን ስድስት ነጥቦች ስሕተት መሆናቸውን የሚያሳይ መሆን አለበት።

፫. ታሪካዊ ማስረጃ ያቅርቡ

ትምህርተ ሥላሴን በሚጻረር መልኩ መሠረተ እምነቴ ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ተብሎ ይጠራል ማለት ብቻ በቂ አይሆንም። ነገረ ግን ክርስትና ክርስቶስ ኢየሱስን የሚያምን ማኅበረሰብ እንደ መሆኑ መጠን፣ ክርስትና ከተቈረቈረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬዎ ቀን ድረስ ለሁለት ሺህ ዓመታት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሃይማኖት ነው። ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ” (ማቴዎስ 28÷19-20) የሚል ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው። ይህ እውነት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመታት ስታምነውና ስታሳምነው የቆየችው መሠረተ እምነት፣ ሥላሴያዊ ነው ወይስ እርሶ ትክክል ነው የሚሉት የሃይማኖት ድርጅት የሚያስተምረው ትምህርት። ለመልሶ ዐጥጋቢ የሆነ ታሪካዊ ማስረጃ ማቅረቦ እርግጠኛ ይሁኑ (የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ፣ ትምህርተ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ስታምነውና ስታሳምነው የቆየችው መሠረተ እምነት ለመሆኑ፣ ከወንድም አማረ መስፍን ጋር በጥምረት ባዘጋጀው መጽሐፍ ላይ በሰፊው ሞግቶአል)።

4. በሥላሴ ትምህርት ውስጥ አለ የሚሉት ስሕተት በእርሶ አማራጭ አስተምህሮ ውስጥ እንደሌለ እርግጠኛ ይሁኑ

ለምሳሌ እርሶ ትምህርተ ሥላሴ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ አረማዊ ተጽእኖ ባላቸው ሰዎች የተጠነሰሰ እምነት ነው የሚሉ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ምን ታምን እንደ ነበር ታሪካን በማጣቀስ ማስረጃዎን ያቅርቡ።

ወይም ደግሞ በትምህርተ ሥላሴ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ቃላት ይገኛሉ ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ እርሶ የሚያቀርቡት ወይም የሚያምኑበት እምነት አስተምህሮውን ለማብራራት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ አንዳችም ቃላት ያለመጠቀሙን እርግጠኛ ይሁኑ።

ትምህርተ ሥላሴ የአረማውያን ሃይማኖቶች ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ፍልስፍና ሰለባ ነው የሚሉ ከሆነ፣ ትምህርተ ሥላሴ ከየትኛው አረማዊ ሃይማኖት ወይም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍልስፍና ትምህርቱን እንደ ቀዳ ያሳዩ። እንዲሁም የእርሶ መሠረተ እምነት ከዚህ ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ነጻ መሆኑን መረጋገጫ ያቅርቡ።

ምናልባት ደግሞ ትምህርተ ሥላሴ ሰዎች ሊረዱት የማይችሉት ወይም ሊረዱት ከባድ የሆነ አስተምህሮ ነው የሚሉ ከሆነ፣ የእርሶ አስተምህሮ እርስ በርሱ ያልተምታታ፣ "ምሥጢር ነው" የሚባልበት አንዳችም ነገር እንደሌለው፣ እንዲሁም ለሥነ አመክንዩ ሕግጋት የተገዛ መሆኑን ማስረጃ ያቅርቡ።

5. የእርሶ መሠረተ እምነት በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ሳይሆን፣ ከትምህርተ ሥላሴ ይልቅ ሁሉንም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማዕከል ያደረገ አስተምህሮ መሆኑን ያሳዩ

አጥባቂያንም ሆኑ ለዘብተኛ አቋም ያላቸው የነገረ መለኮት ሊቃውንት መኻል አብዛኞቹ ምሁራን የሚቀበሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ መሠረት በማድረግ፣ ከአስተምህሮተ ሥላሴ ይልቅ የእርሶ አቋም በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተደገፈ ለመሆኑ ማስረጃ ያቅርቡ። ትክክለኛውን የሥነ አፈታት ሕግ ባልተከተለ መልኩ በጣት በሚቆጠሩ ምንባባት ላይ ብቻ በመቆም፣ "እንቢ ለሃይማኖቴ" ማለት ሳይሆን፣ የሥላሴ አማንያን ለአስተምህሮው ማስረጃነት ከሚያቀርቡት ማስረጃ ይልቅ በርካታ ማስረጃ ለማቅረብ እርግጠኛ ይሁኑ። አንድና ሁለት ምንባባትን ብቻ ይዞ መሠረተ እምነቴ እንዲህና እንዲያ ነው ማለት ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ትክክልኛ ነው የሚሉት አቋም በበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መደገፉንና መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ አስተምህሮ ጋር ያለመጋጨቱን እርግጠኛ መሆን ዋነኛ ጉዳይ ነው።

የሚያቀርቡት ማስረጃ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ፣ የትኛውም የሃይማኖት ክፍል ሊቀበለው የሚችል የዕብራይስጥና የግሪክ ሰዋስው ሕግ፣ የታሪክ ጥናት፣ የሥነ አፈታት ሕግ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍትን በምንጭነት መጠቀሞን ልብ ይበሉ። ይህ ጉዳይ ጥረትዎን ተኣማኒ ድካሞንም ፍሬያማ ያደርገዋል።

መልካም ዕድል እመኝልዎታለሁ!